# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጁን 1-30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ እንዲሁም ከጁላይ ከ1-31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2021
አዲስ አበባ

| ርዕስ | ገፅ |
|---|---|


እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ....................3

ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ....................4

ካርታ 7 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ....................5

ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ....................6

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ....................7

ካርታ 9 ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................7

....................7

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ....................8

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ....................8

....................8

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ....................9

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ .................... 10

እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ.................... 11


# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

ባለፈዉ የጁን ወር የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን ይገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በመዳከሙ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የዝናብ መጠንና ስርጭት ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡ ይሁን እንጂ በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛዉ ሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን በመፈጠሩ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በነዚህ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ከነበረዉ የደመና ሽፋን የበደቡብ ደጋማ ስፍራዎችና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎችም አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፈዉ የጁየን ወር ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች አዲስ አበባን ጨምሮ፤ ጥቂት የምዕራብ አርሲ፣ የባሌ፣ የጉጂ፣ የምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ የደቡብና ሰሜን ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አገዉ አዊ፣ የሰሜን ሸዋ(03)፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ጨምሮ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል እንዲሁም የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ጥቂት የዞን 03ና 05 ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸዉ ጣቢያዎች መካከል አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በአሶሳ 48.6፣ 41.5ና 32.0፣ በጋምቤላ 33.5ና 55.6፣ በማሻ 35.0፣ በእምድበር 62.5፣ 44.6ና 46.0፣ በጉትን 57.5፣ በነጆ 30.0ና 30.9፣ በነቀምቴ 104.2፣ 41.7 እና 38.7፣ በፍቼ 35.5፣ በካቺስ 47.4፣ በኢጃጂ 66.6፣ በአይራ 33.4፣ በጋትራ 52.2፣ በጊምቢ 54.6፣ በቡሬ 30.2፣ በሊሙገነት 31.5ና 68.1፣ በቡሌሆራ 38.8፣ በአልጌ 35.0፣ 30.0ና 30.0፣ በበደሌ በበደሌ 37.0ና 55.4፣ በድዴሳ 71.5፣ በአርጆ 38.4፣ 41.2፣ 44.8፣ 32.6፣ በሶኮሩ 46.0፣ በጅማ 38.5፣ በአዲስ አበባ 41.8፣ በቦሬ 67.2፣ 43.2ና 70.3፣ በማሻ 35.0፣ 65.0፣ 35.0፣ 59.0፣ 49.0፣ 45.8፣ 36.4 እንዲሁም በጂንካ 30.5፣ በተርጫ 35.3፣ በፉኝዶ 43.2፣ በዳንግላ 30.2ና 35.5፣ በቻግኒ 59.5፣ 44.3፣ በሸርቆሌ 63.5፣ በደብረወርቅ 30.5 እና በአይከል 33.7፣ በሚሜ ይገኙበታል፡፡


` ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በቤንሻንጉል ክልል ዞኖች፣ በሰሜን ጎንደር፣ በምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ሸዋ(04)፣ በምዕራብን ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባርና በጅማ፣ በከፋ፣ በሸካና በቤንች ማጂ እነዲሁም በሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከ100-582 ሚሜ የሚደርስ ከ10-24 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በደቡብ ጎንደር፣ በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ(03)፣ በምስራቅ ሸዋ፣ በአርሲና ባሌ፣ በጉጂና ምዕራብ አርሲ፣ በምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በጋሞና ጎፋ፣ በደቡብ ኦሞ፣ በአፋር ክልል ዞነ 03 እና በጋምቤላ ክልል ዞኖች ላይ ከ10-100 ሚሜ የሚደርስ ከ5 ቀናት በታች ዝናብ ነበራቸዉ፡፡

ባለፈዉ የጁን ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በአሶሳና ከማሽ፣ በምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ በሆሮ ጉዱሩ ወለጋ፣ በኢሉባቦርና በጅማ ከጥቂት የምስራቅ ሸዋ በስተቀር በሁሉም የሸዋ ዞኖች ላይ፣ በጥቂት የባሌ፣ በጥቂት የምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች ላይ በአመዛኙ መደበኛ የሆነ የዝናብ ስርጭት ነበራቸዉ፡፡


ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 7   እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 8 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክረዉ ተስተዉሏል፤ በተለይም በምዕራብ አጋማሽና በመካከለኛዉ ሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይበልጥ የተጠናከሩ ከመሆኑም ባሻገር አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደተመዘገበ የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፤ በመሆኑም በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ ዘግይተዉ ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሟሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አነስተኛ የእርጥበት ሁኔታ ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ በተለይም በምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ቢሆንም፤ በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ ያደረሰዉ አሉታዊ ተፅዕኖ አልነበረም (ካርታ 9)፡፡


ካርታ 9 ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ከጁን 1-30/2021 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ባሮአኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌዳዋ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ እና የታችኛዉ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት ሁኔታ የተስተዋለባቸው ናቸው፡፡ የመካከለኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ ስምጥሸለቆ እንዲሁም የላይኛዉ አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ የእርጥበት ሁኔታ እንደነበራቸው ተስተውሏል። የተቀሩት ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደነበር ተስተውሏል (ካርታ 10)።

ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ 30/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር ለወቅቱ ዝናብ መፈጠር መንስኤ የሚሆኑ የአየር ሁኔታ ገፅታዎች መደበኛ ቦታቸዉን የሚይዙበትና የሚጠናከሩበት በመሆኑ የወቅቱ የዝናብ ሥርጭት ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ነጎድጓማ እና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ የሚዘወተርበት እንዲሁም ዝናቡ ለሰዓታት ያለማቋረጥ መዝነብ የሚጀምርበት ወር ነዉ፡፡

በመጪው የጁላይ ወር የክረምት ዝናብ ሰጭ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሜን-ምሥራቅ፣ የደቡብ ደጋማና የምሥራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎችን የሸፈነ ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብ፣ የምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በመሆኑም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል የሚመለከተዉ ሁሉ ከወዲሁ አስፈላጊዉን ጥንቃቄ እንዲደረግ እንመክራለን፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥለው ወር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምስራቅና ምዕራብ ወለጋ፣ ሆሮ ጉዱሩ፣ አርሲ እና ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ከአማራ ክልል ምዕራብና ምሥራቅ ጎጃም፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የዋግ ህምራ እና ሰሜን ሸዋ በተጨማሪም የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች፤ የትግራይ ሁሉም ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጉራጌ፣ የሀዲያ፣ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞ እና የጎፋ ዞኖች፤ የሲዳማ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ያገኛሉ። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ ዝናብ ሊኖር እንደችሚል መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ጉጂ፤ ድሬደዋ እና ሀረሪ፤ የጋምቤላና የቤንሻንጉል ሁሉም ዞኖች፤ ከሶማሌ ክልል የፋፈን እና የኖጎብ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3፣ 4 እና ዞን 5 በተጨማሪም ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል አንዳንድ የደቡብ ኦሞ እና የሰገን ህዝቦች በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ቦታዎች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ይቆያሉ፡፡

# እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ የጁላይ ወር የመኸር እርሻ እንቅስቃሴ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሚከናወንበት ወቅት ሲሆን፤ በተለይም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች እርጥበት የሚስፋፋበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የዘር መዝራት ተግባራት በስፋት የሚከናወንበት ጊዜ ነው፡፡ እንዲሁም አስቀድመው በኤፕሪልና ሜይ ለተዘሩትና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙት የረጅም ጊዜ ሰብሎች ላሉበት ደረጃ የሚያስፈልጋቸውን ውኃ በቂ በሆነ መልኩ የሚያገኙበት ጊዜ ሲሆን፤ በተጨማሪም እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎችም ውኃን ለማከማቸት መልካም አጋጣሚዎችን የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ ከዚህም አልፎ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ አካባቢዎች ለሚከናወኑ የእንስሳት እርባታ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታዎች የሚኖሩበት ጊዜ ነው፡፡

ከላይ በተሰጠው የጁላይ ወር የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው ወር ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን ዝናብ በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ኢትዮጲያ አካባቢዎችን የሸፈነና በአብዛኛው መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር አብቃይ በሆኑትና ዘር መዝራት ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ለዘር ምቹ ሁኔታ እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡ የተሻለ እርጠበት በነበራቸውና ዘር መዝራት በተጠናቀቀባቸው አካባቢዎች በመብቀል ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የሚጠበቀው እርጥበት የተሻለ የውኃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ስለሚያደርግ ለሰብሎቹ እድገት መልካም ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ ሥፍራዎች ላይ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል በማሳ ላይ ዉሃ በመተኛት በቡቃያ ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አስፈላጊው ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ በእርጥበት መብዛት የሚታወቁ አካባቢዎች የማጠንፈፊያ ቦዮችንና የጎርፍ መከላከያ እርከኖችን አስቀድሞ ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ እንዲሁም በእርጥበት መብዛት የሚከሰቱ የሰብል በሽታወችን መቆጣጠር፤ የማደበሪያና ጸረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በጥንቃቄ ማከናዎን ያስፈልጋል፡፡ በአንፃሩ በመደበኛ ሁኔታቸው የእርጥበት እጥረት በሚያጠቃቸው አካባቢዎች በቂ ዝግጅት በማድረግ የሚገኘውን እርጥበት በሰብል ማሳዎች ላይ እንዲቆይ ማድረግና በተጨማሪም ከማሳ ውጪ የውኃ ማሰባሰብ ስራዎች ትኩረት እንዲያገኙ ይመከራል፡፡

በአንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት የመጠጥ ውኃ አቅርቦትንና የእጽዋት የልምላሜ ሁኔታውን እንደሚያሻሽል የሚጠበቅ ቢሆንም፤ የሚገኘውን ውኃ በጥንቃቄ መያዝና በተለያየ መልኩ ከሚከሰት ብክነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ በትንበያው ደረቅ ሆነው እንደሚቀጥሉ በተጠቆሙ አካባቢዎች አማራጭ የእርጥበት ማገኛ መፍትሄወችን ከወዲሁ መመልከት ያስፈልጋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 31/2021 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዉ የጁላይ ወር የክረምት የእርጥበት ሁኔታ በብዙዎቹ የሀገሪቱ የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶዎች ላይ እየተጠናከሩ ሊሄዱ እንደሚችሉና ከዚህም ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ወቅታዊውን የእርጥበት መጠን በመደበኛ ሁኔታ ማግኘት የጀመሩትን የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ተፋሰሶችን ጨምሮ የሰሜን ምሥራቅ እና የምሥራቅ ተፋሰሶዎችን የሸፈነ የእርጥበት ሁኔታ ከመጠበቁም በላይ በአንዳንድ የሰሜን ምዕራብና የመካከለኛዉ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የተሻላ የእርጥበት መጠን እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛው አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ተከዜ፣ ስምጥሸለቆ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛዉና የመካከለኛው ዋቢሸበሌ እንዲሁም አዋሽ ተፋሰሶች ላይ ከበጣም ከፍተኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በሌላ በኩል የላይኛዉ ዋቢሸበሌ፣ የላይኛዉና የመካከለኛዉ ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛዉና የታችኛዉ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የታችኛዉ አባይ፣ የላይኛዉ አፋር ደናከል፣ የታችኛዉ ስምጥሸለቆ እንዲሁም ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። ይህ ሁኔታ ለውሃ ሃብት መጠን መጨመር ጥሩ አስተዋፆ ቢኖረውም፤ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚከሰተው ከባድ ዝናብ በገደላማ ቦታዎች ላይ መሬት መንሸራተትና የወንዞች ሙላት እንዲሁም ለጎርፍ ተጋላጭ ተፋሰሶዎች ላይ ደግሞ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ቅድመ ጥንቃቅ ማድረግ ያስፈልጋል።